# የአቤቱታ አቀራረብ ስርዓት

| ተራ<br>ቁጥር | የአዋጁና መመሪያው<br>አንቀጽ | የአንቀጹ ይዘት | የሚፈጀው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | አዋጅ አንቀጽ ቁ. 68<br>ን.አ4 | ቦርዱ አቤቱታ አጣርቶ ውሣኔ የሚሰጥበት | 10 የሥራ ቀናት |
| 2 | አዋጅ አንቀጽ 67 ን.አ<br>2መመሪያ አንቀጽ 44<br>ን. አ.1ለ | አቤቱታ አቅራቢው ለመ/ቤቱ አቤቱታ ማቅረብ ያለበት | ለአቤቱታው መሠረት የሆነ ውን ጉዳይ ካወ ቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ |
| 3 | .አዋጅ አንቀጽ 67ን.አ3<br>.መመሪያ አንቀጽ 44ን.አ1.ሐ | መ/ቤቱ አቤቱታ ሲቀርብለት አጣርቶ ውሣኔ የሚሰጠው | አቤቱታው በቀረበለት በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ |
| 4 | .አዋጅ አንቀጽ 67ን.አ.4<br>. | ተጫራቹ ለቦርዱ አቤቱታ ማቅረብ ያለበት | መ/ቤቱ ለቀረበው አቤቱታ ምላሽ በጽሁፍ ለአቅራቢው እንዲደርስ ባደረገ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ |
| 5 | .አዋጅ አንቀጽ 67ን.አ.<br>.4 መመሪያ አንቀጽ44ን.አ.1.ሐ | አቤቱታ አቅራቢው ለመ/ቤቱ አቤቱታ አቅርቦ የተሰጠው መልስ ባያረካው ወይም መልስ ባይሰጠው ለቦርዱ አቤቱታ ማቅረብ ያለበት | አቤቱታውን ለቦርዱ ካቀረበ ከ10ኛው የሥራ ቀን በኂላ ባለት 3 የሥራ ቀናት ውስጥ |
| 6 | .አዋጅ አንቀጽ 68 ን.አ.1<br>. መመሪያ አንቀጽ 46 ን.አ.ሀ | ቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብለት መግለጫና ማስረጃ ከመ/ቤቱ የሚጠይቅበት ጊዜ | አቤቱታው እንደቀረበ ወዲያውኑ |
| 7 | መመሪያ አንቀጽ 46 ን.አ.1.ሐ | ቦርዱ አቤቱታ ቀርቦለት መ/ቤቱ መግለጫና ማስረጃ እንዲያቀርብ በቦርዱ ሲጠየቅ ግዥ የተፈፀመባቸውን ሰነዶችን መላክ ያለበት | ማስታወቀያው በደረሰው በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ |
| 8 | መመሪያ አንቀጽ44ን.አ.1 | መ/ቤቱ የጨረታውን ውጤት ወይም የአቤቱታውን ምላሽ | 7 የሥራ ቀናት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ከሰጠ በኋላ ውል ከአሸናፊው ጋር ለመፈረም መጠበቅ ያለበት ጊዜ፣ | |
| 9 | መመሪያ አንቀጽ 47 ን.አ 3 | ቢሮው በአቅራቢ ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት ከመ/ቤቱ ቀርቦለት ለቀረበው ሪፖርት ምላሽ እንዲሰጥ በጽሑፍ ሲጠይቅ ተጫራቹ/አቅራቢው ምላሽ የሚሰጥበት ጊዜ | የማስታወቂያው ደብዳቤ በደረሰው በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ |
| 10 | አዋጅ አንቀጽ 69ን.አ.4 | ቢሮው የጥፋተኛነት ሪፖርቱን አጣርቶ ምላሽ የሚጥበት ጊዜ | የጥፋተኝነት ሪፖርቱ በቀረበለት በ10 የሥራ ቀናት |
| 11 | መመሪያ አንቀጽ 47 ን.አ.4 | ቢሮው አቤቱታውን አጣርቶ ውሣኔውን ለመ/ቤቱ እና የጥፋተኛነት ሪፖርቱ ለቀረበበት ተጫራች እንዲደርስ ማድረግ ያለበት | ብ7 የሥራ ቀናት ውስጥ |

### 4.1.1. በአቤቱታ ላይ ውሳኔ መስጠት

በአዋጁ አንቀጽ 68 መሠረት ቦርዱ በመንግስት ግዢ ወይም ንብረት ማስወገድ አፈፃፀም የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው::

ቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብለት እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል::

ሀ/ በ አቤቱታ አቅራቢው ጥያቄ ቅሬታ የማጣራቱን ሂደት ማቋረጥ፣

ለ/ በሚከተሉት ምክንያቶች የአቤቱታ መዝገቡን መዝጋት፣

1. ጉዳዩ ከሥልጣኑክልል ውጭ ሲሆን፣ **Non – venue**;
2. ጉዳዩ መታየት የማይገባው ሲሆን፣ **Impermissibility**;
3. አቤቱታው በተፈቀደው ጊዜውስጥ ካልቀረበ፣ **Untimeliness,**
4. አቤቱታው ሥልጣን በሌለው ሰው ሲቀርብ፣ lodged by unauthorized person

ሐ/ አቤቱታው መሠረት የሌለው ሲሆን ውድቅ የማድረግ፣

መ/ ሕጉን ያልጠበቀ የመንግስት መ/ቤት ተግባር ወይም ውሳኔን ተፈፃሚ እንዳይሆን ማድረግ፣

ሠ/ በአዋጅና በመመሪያው መሠረት ሊያሠርዝ የሚችል ጉድለት የተገኘበትን የግዥ አፈፃፀም ሂደት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መሠረዝ፣

ረ/ የመንግስት መ/ቤት ሕግን የሚጥስ ተግባር እንዳይፈጸም ወይም ውሳኔእንዳይሰጥ መከልከል፣

ሰ/ ውል ከመሰጠት ወይም ከመዋዋል ውሳኔ በስተቀር አዋጁንና መመሪያውን ተከትሎ እንዲሰራ ለመንግስት መ/ቤት ትዕዛዝ መስጠት፣

**ቦርዱ አቤቱታ በቀረበለት በ10(አሥር ) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለቅሬታ አቅራቢውና ለመንግስት መ/ቤት በጽሑፍ መግለጽ አለበት፣**

ቦርዱ ውሳኔ የሚሰጠው በአቤቱታ ማመልከቻውና በመንግስት መ/ቤቱ ውሳኔ ላይ በተነሱት ጭብጦች ላይ ብቻ ነው።

የቦርዱ ውሳኔ በአባላጫ ድምጽ የሚተላለፍ ሆኖ ለዚሁ ሲባል የተዘጋጀውን ቅጽ በመጠቀም ይፃፋል። ጽህፈት ቤቱ የቦርዱን ውሳኔ ወዲያውኑስ አቤቱታ አቅራቢውና ለሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት ያስተላልፋል። የቦርዱ ውሳኔ የመጨረሻና ተፈፃሚ ይሆናል።

### 4.1.2. የቦርዱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ

የአንድ አቤቱታ ፍሬ ነገር ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት ማንኛውም የቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ መያዝ ያለበት ሲሆን ይህም ቃለ ጉባኤ የሚከተሉትን ያካትታል።

ሀ/ የቃለ ጉባኤውን ቁጥር፣

ለ/ የቦርዱንና የአባላቱን ስም፣

ሐ/ ስብሰባው የተካሄደበትን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት፣

መ/ የግዢውን ወይም ንብረት ሽያጭ መጠሪያ

ሠ/ የአቤቱታውን ፍሬ ነገር፣

ረ/ መ/ቤቱ ለቀረበው አቤቱታ የሰጠውን መግለጫና ያቀረባቸው ሰነዶች ጭብጦች

ሰ/ የተከራካሪ ወገኖችን መቅረብ ወይም ያለመቅረብ የሚመለከት መረጃ በተጨማሪም ቃለ ጉባኤው በቅሬታ ስሚ ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡትን ክርክር እንዲሁም ቦርዱ ስሚ ባለበትም ሆነ በሌለበት ጊዜ የወሰደውን እርምጃ ወይም የሰጠውን ውሳኔ የሚመለከቱ አስፈላጊ መረጃዎችን መያዝ አለበት።

ሸ/ የቦርዱን ትንተናና ውሣኔ፣

ቃለ ጉባኤው በስብሰባው በተገኙ የቦርዱ አባላት መፈረም አለበት፣

ቃለ ጉባኤው የጉዳዩ ማህደር አካል ይሆናል።

### 4.1.3. የቦርዱን ውሳኔ ይፋ ስለማድረግ

ሀ/ ጽሕፈት ቤቱ በያንዳንዱ ውሳኔ የጉዳዩን ፍሬ ነገር፣ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔና ከውሳኔው ላይ የደረሰበትን ምክንያት የሚያሣይ የውሳኔማጠቃለያ መግለጫ ያዘጋጃል፡፡

ለ/ ጽሕፈት ቤቱ ይህንን የውሳኔማጠቃለያ መግለጫ በቢሮው ድህረ ገጽ ላይ በማውጣት ይፋ ያደርጋል፣

ሐ/ ጽሕፈት ቤቱ የውሳኔውን ሙሉ ቃል የያዘውን ኮፒ በመያዝ ውሳኔውን ለማየት ለሚጠይቁ ሁሉ ክፍት ያደርጋል፡፡

## 4.2. በአቅራቢዎችና በተጫራቾች ላይ በመንግሥት መ/ቤት የሚቀርብ የጥፋተኝነት ሪፖርት ስለማጣራት፣

ሀ/ በመግስት ግዥ ወይም ንብረት ማስወገድ ተሳታፊ የሆነ አንድ ተጫራች ወይም አቅራቢ አዋጁን ወይም መመሪያውን መጣሱን፣ አሸናፊ የሆነበትን ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ያለመሆኑን፣ የማጭበርበር ድርጊት መፈጸሙን ወይም ሐሰተኛ ሰነድ ማቅረቡን፣ የመመሣጠር ወይም የሙስና ተግባር መፈጸሙን ወይም በገባው ውል መሠረት ያለበትን ግዴታ ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማረጋገጥ የሚችል የመንግስት መ/ቤት በአቅራቢው ወይም በተጫራቹ ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቢሮው ማቅረብ ይችላል፡፡

ለ/ የመንግስት መ/ቤት በአንድ ተጫራች ወይም አቅራቢ ላይ ለቢሮው የጥፋተኝነት ሪፖርት ሲያቀርብ አቅራቢው ወይም ተጫራቹ የፈጸመውን የጥፋት ዓይነት በመግለጽ ጥፋቱ የተፈጸሙበትን ግዥ ወይም ንብረት ማስወገድ አፈፃፀም የሚያሣየውን የግዥ ወይም ንብረት ማስወገድ እና ሌሎች ሰነዶች እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሰነዶች ከሪፖርቱ ጋር አባሪ አድርጐ ማቅረብ አለበት፡፡